# ስለ SBS መርሃ ግብር



SBS **በቻርተራችን** ውስጥ እንደሰፈረው ከኃላፊነቶች ጋር ነፃና ገለልተኛ የሆነ ብሔራዊ የሕዝብ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮና ዲጂታል ሚዲያ ግልጋሎት ሰጪ ነው። የምንደጎመውም በአውስትራሊያ መንግሥትና ማስታወቂያን በመሰለ የንግድ ገቢ ነው።

በመላው አውታረ መረባችን ልዩ የአውስትራሊያን ትርክቶች፣ የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ዜናዎችንና ወቅታዊ ጉዳዮችን፣ ስፖርት፣ ዓለም አቀፍ ድራማዎች፣ ዘጋቢ ፊልሞች፣ ምግብ፣ ፊልምና የአገር ውስጥ ሬዲዮ ግልጋሎቶችን ከ60 በላይ በሆኑ ቋንቋዎች እናጋራለን። እንዲሁም ከብሔራዊ ነባር ዜጎች ቴሌቪዥን ጋር በነባር ዜጎች አጉሊ መነጽሮች ዕይታ ፕሮግራሞችን እናቀርባለን። የነባር ዜጎች ትርክቶች መገኛ ነን።

በቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ኦንላይን ወይም በማኅበራዊ ሚዲያ ይከታተሉት፤ ሁሉም ይዘት የማኅበረሰብ ደረጃን የጠበቀ እንዲሆን፣ የSBS ደንቦችና ደረጃዎችን የሚያስጠብቅ የ SBS መርሃ ግብር አለን።

## መርሃ ግብሩ ጠቃሚ ጉዳዮችን ይሸፍናል፤ እንደ

### ተአማኒነት

**እንደምን ተአማኒነት የሚጣልበትንና ፋይዳ ያለውን ይዘት እንደምናቀርብ**

- ይዘታችንን አስመልክቶ ነፃና ገለልተኛ ከሆኑ ውሳኔዎች ላይ እንደርሳለን
- የዜናዎቻችንና ወቅታዊ ጉዳዮቻችን ይዘት ከሕዝባዊ ጠቀሜታ አኳያ ሚዛናዊና አድሎአዊ ያልሆኑ ናቸው
- የተለያዩ አተያዮችንና ምልከታዎችን እናካትታለን፤ ይዘታችን በዓይነቱ አዲስና አዋኪ እንዲሁም አወዛጋቢና ጎንታይ ሊሆን ይችላል

### ግልጽነት

**የእርስዎን የይዘት ምርጫዎች እንደምን አመላከተን እገዛ እንደምናደርግ**

- እኛ መረጃን እናቀርባለን እርስዎ ለእርስዎና በእርስዎ ክብካቤ ስር ላሉ ልጆችና ወጣቶች ተገቢ የሚሆነውን ይዘት ይመርጣሉ
- ለየት ያሉ ማስታወቂያዎች ከእኛ ይዘትና የሰፈሩ ደንቦች እንዲነጠሉና እንዲተኩ እናደርጋለን
- አዋኪነትን የተላበሰ ይዘት ያለ ዝግጅት የሚቀርበው የአርትዖት ፋይዳ ያለው ብቻ ሲሆን ይሆናል፤ እንደሁኔታውም ታዳሚዎች ተጨማሪ ጥንቃቄን እንዲያደርጉ እናሳስባለን

### ከበሬታ

**ከበሬታን እንደምን ግብር ላይ እንደምናውልና እንደምናስተዋውቅ**

- ፍትሐዊነትን ያልተላበሱ የጅምላ የተዛባ አመለካከትን አካትቶ፤ ጭፍን ጥላቻንና አግላይነትን ያዘለ ይዘትን እንከላለን
- ከእንግሊዝኛ ሌላ በሆኑ ቋንቋዎች ይዘቶችን እናቀርባለን፤ እንዲሁም የተለያዩ ዓይነት አመለካከቶች እንዲንፀባረቁ እናበረታታለን
- የነባር ዜጎች ጉዳዮችን ስናቀርብ ለአቦርጂናልና ቶረስ ስምጥ ደሴት ሕዝቦች ባሕላዊ ፕሮቶኮሎች በእጅጉ ጥንቃቄን እናደርጋለን
- የሰዎችን ገመና እናከብራለን፣ ከዘገባ ኃላፊነቶቻችን ጋር ሚዛን እናስጠብቃለን

### ተጠያቂነት

**ተጠያቂነታችን እንደምን ነው**

- ስለ ይዘትና ግልጋሎቶቻችን መልካምነትም ሆነ ነቀፌታ ግብረ ምላሽ እንዲሰጡን ሁኔታዎችን እናመቻቻለን
- መርሃ ግብርን ተከትሎ ቅሬታዎች በ SBS ዕምባ ጠባቂ የሚመረመርበት ነፃና ገለልተኛ ሂደት አለን




SBS

ተጨማሪ ካሹ
sbs.com.au/aboutus/sbs-code-of-practice